# መንግስት በህይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነት እና የመዘዋወር መብቶችን በተገቢው ሁኔታ ሊያከብር እና ሊያስከብር ይገባል!

ታህሳስ 08/2015 ዓ.ም

## መግቢያ፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህዳር 03 ቀን 2015 ዓ.ም ምዕራብ ጎጃም ዞን ሰሜን አቸፈር ወረዳ ሽብላ ባኩልቲ በተባለ ቀበሌ ውስጥ ሶስት ወጣት የቀበሌው ነዋሪዎች የቀበ ሌዉን የወል መሬት የቀበሌዉ አስተዳዳሪ ለግል ጥቅሙ ለማዋል ሙከራ በሚያደርግበት ጊዜ ድርጊቱን በመቃወማቸዉ በቀበሌዉ አስተዳዳሪና በግብረ አበሮቹ በአሰቃቂ ሁኔታ በጥይት መገደላቸውን እና ይህንን ድርጊት የፈጸሙት አካላት ይህ ሪፖርት እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ምንም አይነት የህግ ተጠያቂነት እንዳልተመሰረተባቸው ኢሰመጉ ከቀረቡለት አቤቱታዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ውስጥ በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ከመምህራን እና ረዳት መምህራን ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም ጋር ተያይዞ የተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን እና ረዳት መምህራን ለተወሰነ ጊዜ የስራ ማቆም አድማ አድርገው እንደነበረ እና የተማሪዎች ትምህርት እንዳይስተጓጎል በሚል ወደ ስራ ገበታቸው እንደተመለሱ እና ጥያቄያቸውን በተመለከተ በህጋዊ መንገድ መጠየቅ የሚቀጥሉ መሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡ ከእዚህም ጋር ተያይዞ ሶስት የአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ መምህራን አድማ አስተባብራችኋል በሚል ህዳር 26 ቀን 2015 ዓ.ም ታስረው በታህሳስ 03 ቀን 2015 ዓ.ም መለቀቃቸውን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች በተደጋጋሚ በሚነሱ ግጭቶች በርካታ ሰዎች ላይ ሞት፣ የአካል ጉዳት፣ ጾታዊ ጥቃት፣ ንብረት ውድመት፣ መፈናቀል እና ሌሎችም ዘርፈ ብዙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሲፈጸሙ  ቆይተዋል፡፡ ኢሰመጉ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ችግሩ ከቁጥጥር ውጪ ሳይወጣ መንግስት ዘላቂ መፍትሔ በማፈላለግ የሰዎችን ሰብዓዊ መብቶች እንዲያከብር፣ እንዲያስከብር እና እንዲያሟላ ሲወተውት ቆይቷል፡፡ ነገር ግን በክልሉ አሁንም በታጣቂዎች የሚፈጸሙ ሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ከምንጊዜውም በላይ እየጨመሩ ይገኛሉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኦሮሚያ ክልል ሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ውስጥ በሚገኙ አሙሩ፣ ጃርቴ ጃርደጋ፣ ኦዳ ቡሉቅ እና ከፊል አበዶንጎሮ ወረዳዎች እንዲሁም በምስራቅ ወለጋ ዞን ውስጥ በሚገኙት ጉቶ ጊዳ፣ ሳስጋ፣ ጊዳ አያና፣ ሀሮ ሊሙ፣ ኤባንቱ እና ኪረሙ ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ ቀበሌዎች በሚንቀሳቀሱ በርካታ የታጠቁ ቡድኖች የመንግስትንም የጸጥታ ሀይል ጨምሮ በሚየደርጉት ግጭት በርካታ ሰዎች ላይ ሞት፣ የአካል ጉዳት፣ ጾታዊ ጥቃት፣ ንብረት ውድመት እና መፈናቀል እየደረሰ እንደሆነ እና ይህ ችግር አሁንም ድረስ ቀጥሎ እንደሚገኝ ኢሰመጉ ከአካባቢዎቹ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡ ይህ ግጭት እየተባባሰ ሄዶ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን ከኪረሙ እስከ ጊዳ አያና (ጉትን) ወረዳዎች ድረስ፣ በሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ከሀሮ ቡሉቅ ወረዳ እስከ ጃርጋ ጃርቴ እና ኡሙሩ ወረዳዎች መስፋፋቱን እና በእዚህም ምክንያት በርካታ ያልታጠቁ ንፁሃን ሰዎች ላይ ሞት፣ የአካል ጉዳት፣ ጾታዊ ጥቃት፣ ንብረት ውድመት እና መፈናቀል እየደረሰ እንደሆነ ኢሰመጉ ተረድቷል  ፡፡

በክልሉ አስቀድሞ ከነበሩ ተፈቃናያዎች በተጨማሪ በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ውስጥ ከሚገኙት አሙሩ፣ ጃርቴ ጃርደጋ፣ ኦዳ ቡሉቅ እና ከፊል አበዶንጎሮ ወረዳዎች ውስጥ በሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ቡድኖች የመንግስትንም የጸጥታ ሀይል ጨምሮ በመካከላቸው በሚፈጠር ግጭት የተፈናቀሉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሻምቡ ከተማ ጃን ሜዳ እና ጤና ጣቢያ በሚባሉ አካባቢዎች ላይ ተጠልለው እንደሚገኙ፣ የተወሰኑትን በ29/03/2015 ዓ.ም ወደ መጡበት አካባቢ ለመመለስ ሙከራ በሚደረግበት ወቅት በመንገድ ላይ ጥቃት እንደተፈጸመባቸው እና ተፈናቅለው ወደተጠለሉበት አካባቢ እንደተመለሱ ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡ በተጨማሪም በኪረሙ ወረዳ በተፈጠረ ግጭት እና በተፈጸመ ጥቃት በወረዳው ይኖሩ የነበሩ እስከ ሰላሳ ሺ (30,000) የሚደርሱ ንፁሃን ሰዎች ተፈናቅለው ጊዳ አያና እንደተጠለሉ እና ለእነዚህ ተፈናቃዮች የሚደርሰው ሰብዓዊ ድጋፍ በአካባቢው የጸጥታ ችግር ምክንያት እጅግ አነስተኛ እንደሆነ ኢሰመጉ ከአካባቢዎቹ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡ በምስራቅ ወለጋ በኑኑ ቁምባ ወረዳ አዳሬ በሚባል አካባቢ ዋማ ጉዳቱ እና ዋማ ዶሼ ቀበሌዎች ውስጥ በ20/03/2015 ዓ.ም እና በ21/03/2015 ዓ.ም በመንግስት የጸጥታ ሀይል እና በታጣቂ ቡድኖች መካከል በነበረ ግጭት ምክንያት በመንግስት የጸጥታ ሀይሎች እንዲሁም በታጣቂ ቡድኖቹ በተፈጸመ ጥቃት በአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ፈይሳ ኢታና፣ ዱጉማ ሽፈራ፣ ታሪኩ ወርቁ፣ ግርማ ገዳ እና ተመስገን ኪዳኔ የተባሉ ሰዎች የተገደሉ ሲሆን በሌሎች ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት፣ ንብረት ውድመት እንዲሁም የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መፈጸማቸውን ኢሰመጉ  ተረድቷል፡፡

በተጨማሪም ህዳር 25 ቀን 2012 ዓ.ም 17 የደምቢዶሎ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በሸኔ ታጣቂ ቡድን ታግተው እንደነበር እና ይህ መግለጫ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ያሉበት እንደማይታወቅ ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት የቻለ ሲሆን እንዲሁም ህዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም የደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን እንዲሁም ሌሎች መንገደኞችን ይዞ ሲጓዝ የነበረ ባስ ምዕራብ ወለጋ ጊምቢ ከተማ አካባቢ በሸኔ ታጣቂ ቡድኖች እንዲቆም ከተደረገ በኋላ በባስ ውስጥ ተሳፍረው የነበሩ ከዘጠኝ በላይ የሆኑ የደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ታጣቂ ቡድኑ አግቶ ከወሰደ በኋላ ይጓዙበት የነበረውን የኦዳ ባስ ማቃጠሉን እና ይህ መግለጫ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ታግተው የተወሰዱት ተማሪዎች ያሉበትን ማወቅ እንዳልተቻለ ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች  ተገንዝቧል፡፡

## ተያያዥ የህግ ግዴታዎች፡

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀጽ 3፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳንም (ICCPR) በአንቀጽ 6(1) እና 9(1) ላይ እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት እንዳለው ያረጋግጣል። ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት

በቃል-ኪዳኑ (ICCPR) የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2(1) እና 2(2)ይደነግጋል።

የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች (ACHPR) አንቀጽ 4 ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት መብቱ ሊከበርለትና ሊጠበቅለት እንደሚገባና እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፈግ እንደማይችል ተመላክቷል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 14"ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው" ሲል ይደነግጋል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 15 ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ ከተደነገገው ውጪ ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይችል በግልፅ ደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀጽ 16 ላይ ማ ንም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው ሲል ያስቀምጣል፡፡

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀጽ 13፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳንም (ICCPR) አንቀጽ 12 ላይ በአንድ አገር ግዛት ውስጥ በሕጋዊ መንገድ ያለ ማንኛውም ሰው በዚያ አገር ውስጥ በነጻነት የመንቀሳቀስ መብት እንዳለው ይደነግጋሉ፡፡ የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች (ACHPR) አንቀጽ 6 ላይ ማንኛውም ሰው ነጻነቱና አካላዊ ደህንነቱ ተጠብቆለት የመኖር መብት አለው ሲል ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀጽ 17 እና 32 ላይ ማንኛውም ሰው የአካል ነጻነት መብት እንዳለው እና በነጻነት በፈለገው አካባቢ የመዘዋወር መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ አባል ሀገር ባትሆንም ሰዎችን አስገድዶ ከመሰወር ለመጠበቅ የወጣው ዓለም አቀፍ ስምምነት(International Convention for the Protection of All Persons from Enforced Disappearance) በአንቀጽ 1(1) ላይ ማንም ሰው ለአስገድዶ መሰወር ተጋላጭ መሆን እንደሌለበት በመደንገግ ይህንን ወንጀል የፈጸሙ አካላትን መንግስት በወንጀል ተጠያቂ እንዲያደርጋቸው ይደነግጋል፡፡

## የኢሰመጉ ጥሪ፡

- መንግስት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ጎጃም ዞን ሰሜን አቸፈር ወረዳ ሸብላ ባኩልቲ በተባለ ቀበሌ ውስጥ ሶስት ወጣት የቀበሌው ነዋሪዎችን ስልጣናቸውን መመኪያ በማድረግ ከህግ አግባብ ውጪ የሆነ ግድያ (extra judicial killing) የፈጸሙ የመንግስት አመራሮችን በህግ ተጠያቂ በማድረግ ወንጀል ሰርቶ ተጠያቂ ያለመሆን ልማድን (culture of impunity) እንዲያስቀር፣
- በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ውስጥ በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ከመምህራን እና ረዳት መምህራን ደሞዝ እና ጥቅማ ጥቅም ጋር ተያይዞ ያሉ አለመግባባቶች እና በመምህራን ላይ የሚፈጸሙ እስሮች የመምህራኑን መብት እና ግዴታ ባገናዘበ መልኩ እንዲፈቱ፣
- በተደጋጋሚ ኦሮሚያ ክልል ሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ውስጥ በሚገኙ አሙሩ፣ ጃርቴ ጃርዳጋ፣ ኦዳ ቡሉቅ እና ከፊል አበዶንጎሮ ወረዳዎች እንዲሁም በምስራቅ ወለጋ ዞን ውስጥ በሚገኙት ጉቶ ጊዳ፣ ሳስጋ፣ ጊዳ አያና፣ ሀሮ ሊሙ፣ ኤባንቱ እና ኪረሙ ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ ቀበሌዎች ውስጥ በሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ቡድኖች የመንግስትንም የጸጥታ ሀይል ጨምሮ የሚፈጸሙ ዘርፈ ብዙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ዘላቂ ሰላማዊ መፍትሄ እንዲያበጅ እና በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎችን ለአመታት የቆየ ስጋት እንዲያስቆም፣
- በኦሮሚያ ክልል ሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ውስጥ በሚገኙ አሙሩ፣ ጃርቴ ጃርዳጋ፣ ኦዳ ቡሉቅ እና ከፊል አበዶንጎሮ ወረዳዎች እንዲሁም በምስራቅ ወለጋ ዞን ውስጥ በሚገኙት ጉቶ ጊዳ፣ ሳስጋ፣ ጊዳ አያና፣ ሀሮ ሊሙ፣ ኤባንቱ እና ኪረሙ ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ ቀበሌዎች ውስጥ የሚደርሱ ግጭቶችን ተከትሎ ተፈናቅለው በተለያዩ የኦሮሚያ እና የአማራ ክልል አካባቢዎች ውስጥ ተጠልለው ለሚገኙ ሰዎች መንግስት አፋጣኝ የሆነ የሰብዓዊ እርዳታ እንዲያቀርብ እንዲሁም ሌሎች ዓለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍ እና የሀገር ውስጥ ረጂ ድርጅቶች ለእነዚህ ተፈናቃዮች ድጋፍ እንዲያደርጉ እንዲጠይቅ፣
- ህዳር 25 ቀን 2012 ዓ.ም የታገቱ 17 የደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እና ህዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም ከዘጠኝ በላይ የሆኑ በሸኔ ታጣቂ ቡድን የታገቱ የደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን መንግስት በሰላማዊ መንገድ እንዲያስለቅቅ እንዲሁም የአካባቢውን ሰላም በማረጋገጥ የመንገደኞችን ደህንነት እንዲያስጠብቅ፣
- በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች በዋናነት በሆሩ ጉድሩ ወለጋ ዞን እና በምስራቅ ወለጋ ዞን ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች ውስጥ የሚነሱ ግጭቶችን እና እነዚህንም ግጭቶች ተከተሎ የሚነሱ ጥቃቶችን እና የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የማስቆም ተቀዳሚ ኃላፊነት በኦሮሚያ ክልል መንግስት እና በፌደራል መንግስት ላይ የሚወድቅ መሆኑን የሚመለከታቸው የሁለቱ የመንግስት አካላት በመረዳት የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች የማክበር፣ የማስከበር እና የማሟላት ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ በተጨማሪም በእዚህ ጉዳይ ላይ ትርፍ ለማግኘት እየሰሩ ያሉ እና ለችግሩ መባባስ አጃቸው ያለበት የመንግስት አመራሮችን በአፋጣኝ በማጣራት የኦሮሚያ ክልል መንግስት እንዲሁም የፌደራል መንግስት በህግ ተጠያቂ እንዲያደርግ፣
- የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን በኢትዮጵያ በሚገኙ የተለያዩ የፖለቲካ እና የሃሳብ መሪዎች እንዱሁም የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሃሳብ ልዩነት እና አለመግባባት መኖሩን በማመን ይህንን ልዩነት እና አለመግባባት ለመፍታት ሰ ፋፊ ሀገራዊ የሕዝብ ምክክሮችን አካታች በሆነ መንገድ በማካሄድ ሀገራዊ መግባባት መፍጠር አንዱ የተቋቋመበት አላማ በመሆኑ በእዚህ አላማ መሰረት በኦሮሚያ ክልል እየተፈጠሩ ያሉ መጠነ ሰፊ ችግሮችን በቂ ትኩረት እና ቅድሚያ በመስጠት እንዲሰራበት፣
- በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በተደጋጋሚ ጊዜ በተደራጀ መልኩ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን በማስቆም ረገድ የሀይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ሲቪል ማህበራት፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ጋዜጠኞች እና ሚዲያዎች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ እና መንግስትም ኃላፊነቱን በቂ ትኩረት ሰጥቶ እንዲወጣ እንዲወተውቱ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ